# የእንቁጣጣሽ ዋዜማ በዐል
# በካናዳ ቫንኮቨር ከተማ ተከበረ።

የዘመን መለወጫ ዋዜማ በዐል ጷግሜ 5 ቀን 2005 ዓም ማክሰኞ ከምሽቱ 2፡00 ጀምሮ እስከ ምሽቱ 6፡00 እኩለ ሌሊት ድረስ በቼሊ ኮምዩኒቲ መሰብሰቢያ አዳራሽ በርካታ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት ለመጀመሪያ ጊዜ በድምቀት ተከበረ።

በኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ በዐል አከባበር ባህልና ወግ መሰረት በአገር ውስጥ እንደሚደረገው ሁሉ ከእራት ግብዣው በኋላ የችቦ ማብራት ስነ ስርዐት ሁሉም በተጋባዥ እንግዶችና አዘጋጆቹም ችቦው ከበራ በኋላ 'አበባ አየሽወይ' የእንቁጣጣሽ ዜማ የሚያዜሙ ልጃገረዶች ለበዐሉ ከፍተኛ ድምቀት ከመስጠታቸውም በላይ ዜማውን ያዜሙት በሙሉ ከኢትዮጵያ ውጪ የተወለዱ በመሆናቸው ኢትዮጵያዊነት ምን ያህል በዚህ ትውልድ መስረጹንና በብዙ ታዳሚዎች ከፍተኛ አድንቆትና ትውስታን ፈጥሯል።

በበዐሉ ላይ የልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ብሔረሰብ ዜማና ውዝዋዜ ቀርቦ ነበር። የቴዲ አፍሮ 'አበባ አየሁሽ' እና የጉራጌ ሀገረሰብ ባህላዊ ሙዚቃና ጭፈራ ለዋዜማው ትልቅ ድምቀት ሰጥተውት አምሽተዋል። ወጣቶቹ ደረጃውን የጠበቀ ባህላዊ ጭፈራ ልምድ ያገኙት 'ውቢት ኢትዮጵያ' በሚል ስያሜ ተቋቁሞ በነበረ የኪነት ቡድን እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

በዐሉን ያዘጋጀው 'የመላው ኢትዮጵያ አንደነት ድርጅት (መኢአድ)' ድጋፍ ኮሚቴ በቫንኮቨር አስተባባሪነትና እንዲሁም የ ኢሕአፓ፤ ግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን፤ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲና ግለሰቦች ትብብር ነው።

በበዐሉ ላይ ያዘጋጅ ኮሚቴው ሰበሳቢ እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ስለ እንቁጣጣሽ በዐል ምክናያት፤ የጋራ ባህልና የአብሮነትን ጥቅም አስረድተው ለአዘጋጆቹና በበዐሉ ላይ ለተገኙት እንግዶች ምስጋና አቅርበዋል። የኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ ፕሬዚዳንትም ባደረጉት ንግግር በጋራ የመሰባሰብ ጥቅምና አንድነት የጥንካሬያችን መሰረት መሆኑን አሰረድተው እንደዚህ ያለው ሕብረት እንዲቀጥል አሳስበዋል። በመጨረሻም ሻምፓኝ ከተከፈተ በኋላ ጨዋታው ቀጥሎ ከሌሊቱ 6ሰዐት ሲሆን ለሚቀጠለው ዓመት ለመገናኘት ተወስኖ በሽማግሌዎች ምርቃት በሰላም ተጠናቋል።